ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ሲቪክ ድርጅት በአውሮፓ

MORESH WEGENIE AMARA CIVIC ORGANIZATION IN EUROPE

!!! የስብሰባ ጥሪ !!!

ሞረሽ ወገኔ አማራ ሲቪክ ድርጅት በአውሮፓ(ሞወአሲድ አ) በተለያዩ የአውሮጳ ከተማዎች በየከተማው ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በየሐገሩ ካሉ ማህበራት ጋር በመተባበር ታላቅ ሕዝባዊ ስብሰባ ያዘጋጀ መሆኑን ያስታውቃል።

ስዊድን ፡ ስቶክሆልም August 2 2014 , ከ13:00 እስከ 20:00 CET,

Hallunda Folkets Hus

ጀርመን ፡ ፍራክፈርት August 9 2014,ከ 13:00 – 18:00 CET,

Bürgerhäuser Dreieich,Fichtestraße

50 63303 Dreieich

ሆላንድ፡ አምስተርዳም August 10, in Amsterdam

እንግሊዝ ፡ ሎንደን August 17 2014 2:00 PM, ECB HALL, 2A

LITHOS ROAD, FINCHLAY ROAD,

LONDON NW3 6EF

በዚህ ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ **አቶ ተክሌ የሻው የሞረሽ ወገኔ ሊቀ መንበርን** የጋበዘ መሆኑን እየገለጸ፣ ስለ አማራው ሕዝብ የስቆቃ ኑሮ እንዲሁም ስለ ሞረሽ ወገኔ ዐማራ ድርጅት ወቅታዊ መግለጫ እንደሚሰጡ ይጠበቃል ።

ለአለፉት 23 ዓመታት የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጭ ድርጅት አማራውን በዋና ጠላትነት ፈርጆ ከየትኛውም የሐገሪቱ ክፍል ለማጽዳት ከፍተኛ የሆነ የዘር ማጥፋት ዘመቻ ከፍቶበታል።

ኢትዮጵያን ኢትዮጵያ የሚያደርጋትን ታሪካዊ ቅርሶችና የብሔራዊ ማንነታችን መሰረት የሆኑትን ጥሪቶች ሁሉ አጥፍቶ ያልነበረች ሐገርና ሕዝብ ለመፍጠር ሌት ከቀን የሚያደርገውን ሥር የሰደደ ዘመቻ ዳር ለማድረስ እንዲችል ዐማራውን ከምድረ ኢትዮጵያ ለማጥፋት ሁለገብ ጥቃት ከፍቶበት ይገኛል።

ይህ ሆን ተብሎ በትግራይ ነጻ አውጭ ድርጅት የተነደፈ ፖሊሲ፣ ዐማራውን መምታት እና ኢትዮጵያዊነትን ማዳከም ዘመቻ በዝምታ ከታዬ ለዘመናት በልጆችዋ ተጋድሎ ተከብራ የኖረችውን ሐገራችንን ከምድረ ገጽ የሚያጠፋ ከመሆኑም በላይ ለሀገራችንና ለሕዝባችን በየትኛውም የሐገሪቱ ክፍል በሰላም ተከባብሮ በአንድነት የመኖር ተስፋ ከፍተኛ አደጋ ላይ ጥሎት ይገኛል።

ይህን አደጋ በመገንዘብ የዜግነት ድርሻውን የማበርከት ጽኑ እምነት ያለው ሁሉ በዚህ ሕዝባዊ ስብሰባ በመገኘት ወገናዊ ጥሪውን ምላሽ ለመስጠት ድርሻውን እንዲያበረክት ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ፈለገ አስራት የትውልዳችን ቃል ኪዳን ነው!!!

ሞወዐሲአ